እንዲህ ሊባል ይችላል፡-

الرِّسَالَةُ المُنْجِدَة

في حَلِّ ألفَاظِ

العَقِيْدَةِ المُرْشِدَة

في بَيَانِ عَقِيدَةِ أَهْلِ السُّنَّةِ وَالجَمَاعَةِ

ኦርፈሳለቱል ሙንጂዳህ

የዓቂደቱል ሙርሺዳህ የቃላት ፍቺ

የአህሉሱና ወልጀማዓህ እምነት ብያኔ

للشَّيْخ علِيّ بن عَدْنَان الشَّافِعِيّ القَادِرِيّ

غَفَرَ اللهُ لَهُ وَلِوَالِدَيْه

ለሼኽ ዓሊ ኢብን ዓድናን አሸሻፊዒይ አልቃድሪይ

ለአርሱና ለወላጆቹ አሏህ ይማራቸው

የመጀመሪያው እትም

1434 ዓ.ሂ - 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

مسودة

مَتْنُ العَقِيْدَةِ المُرْشِدَةِ

የዓቂደቱል ሙርሺዳህ መትን

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

አሏህ እኛንም ሆነ አንተን ወደ ቀና መንገድ ይምራን። ሀያሉና ታላቁ ፈጣሪያችን አሏህ በንግስናው ብቸኛ መሆኑን በተጠያቂዎች ሁሉ ማወቁ ግዴታ መሆኑን እወቅ። ዓለምን በጠቅላላ፣ ላይኛውንና ታችኛውን ክፍል፣ ዓርሽና ኩርስይን፣ ሰማያትንና መሬትን፣ ውስጣቸውና መካከላቸው ያለውን ሁሉ ፈጠረ። ሁሉም ፍጥረታቶች በችሎታው ቁጥጥር ሥር ናቸው። ቅንጣትም ብትሆን ካለ እርሱ ትእዛዝ አትንቀሳቀስም። ከእርሱ ጋር ፍጡርን የሚያስተዳድር የለም። በንግስናውም አጋር የለውም። ሕያው እንዲሁም በእራሱ የተብቃቃ፤ ማንቀላፋትም ሆነ እንቅልፍም አይወስደውም። የተደበቀውንም ሆነ የሚታየውንም የሚያውቅ ነው። በምድርም ሆነ በሰማይ ምንም አይሰወርበትም። በየብስና በባህር ውስጥ ያለውን ያውቃል። አንዲትም ቅጠል ብትሆን አትወድቅም እርሱ ሳያውቃት። አንዲትም ፍሬ ብትሆን ጨለማ መሬት ላይ፣ እርጥብም ሆነ ደረቅ አይኖርም ለውሐል ማህፉዝ ውስጥ ቢኖር እንጂ። ሁሉንም ነገር በእውቀቱ አካቷል። የሁሉንም ነገር ብዛት ያውቃል። ያሻውን የሚያደርግ፤ በሚፈልገው ነገር ላይ ችሎታ አለው። ንግስናም አለው እንዲሁም በራስ መብቃቃት። የማይበገር ሀይልም አለው፤ እንዲሁም ዘላለማዊነት። ፍርድም አለው አንዲሁም ውሳኔ። መልካም ስሞችም አሉት። የወሰነውን የሚመልስ የለም። የሰጠውንም የሚከለክል የለም። በፍጥረቱ የፈለገውን ያደርጋል። ፍጥረቱ ላይ በሚፈልገው ይፈርዳል። ምንዳም አይጠብቅም። ቅጣትም አይፈራም። በእርሱ ላይ ግዴታም ሆነ ፍርድ የለበትም። ፀጋዎች ሁሉ ከእርሱ ችሮታ ነው። ቅጣቶቹ ሁሉ ከእርሱ ፍትህ ነው። በሚሰራው አይጠየቅም እነሱ ግን ይጠየቃሉ። ከፍጥረታት በፊት የነበረ ነው። ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ የሚባል የለውም። ላይም ሆነ ታች፣ ቀኝም ሆነ ግራ፣ ፊትም ሆነ ጀርባ የለውም። የዓለም አጠቃላይም ሆነ ከፊሉም አይደለም። መቼ ነበር አይባልም። የት ነበርም ሆነ እንዴት ነበር አይባልም።

ቦታ ሳይኖር ነበር። ፍጥረታቶችንም ከወነ። ዘመንንም አበጀ። በዘመን አይታጠርም። በቦታም አይወሰንም። አንድ ጉዳይ ከሌላ ጉዳይ አይጠምደውም። ሐሳብ አይደርስበትም። ልቦናም አያካልለውም። በጭንቅላት ውስጥም አይወሰንም። በነፍስም ውስጥ አይመሰልም። በሐሳብም አይሳልም። በልቦናም እንዴት ተብሎ አይታሰብም። ሐሳብም ሆነ ቅዠት አይደርስበትም። እርሱን የሚመስል በጭራሽ የለም። ﴿እርሱ ሰሚም ተመልካችም ነው﴾።

الرِّسَالَةُ المُنْجِدَة

فِي حَلِّ أَلفَاظِ العَقِيْدَةِ المُرْشِدَة

አርሪሳለቱል ሙንጂዳህ

የዓቂደቱል ሙርሺዳህ የቃላት ፍቺ

<u>መግቢያ</u>

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ምስጋና ለአሏህ ይገባው፡፡ ሶላትና ሰላም በአይነታችን በሙሐመድ እና በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም መልካምና ንጹህ በሆኑት በሰሀቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡

በመቀጠልም ዓሊሙ ሼኽ ፈኽሩዲን ኢብኑ ዓሳኪር[1] አሏህ ይዘንላቸውና ሲያስተምሩበት የታወቀው መጽሐፍ ‹‹አል-ዓቂደቱል ሙርሺዳህ›› የአህሉሱና ወልጀማዓን እምነት በትክክለኛ መንገድ ቀላልና አሻሚ ባልሆኑ ቃላቶች የሚያብራራ አጠር ያለ ጽሁፍ ነው፡፡ ለዚህም ነው በብዙ አገሮች የመሰራጨት እድል ያገኘው፡፡ ትንሾችም ሆነ ትልቆች እንዲማሩት ተደረገ፡፡ ለጀማሪ ተማሪ የመጽሐፉንም ትርጉም በይበልጥ ሊረዳ ዘንድ ከመትኑ ጋር የተቀላቀለ አጠር ያለ ትንታኔ በያዘ መልኩ ለቃላቶቹ ፍቺ አበጅንለት፡፡ መጽሐፉንም ‹‹አርሪሳለተል ሙንጂዳህ ፊ ሐሊ አልፋዚል ዓቂደቲል ሙርሺዳህ›› በማለት ሰየምነው፡፡ አሁን የመጽሐፉን ትንታኔ የምንጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ አሏህ መልካም ስራን ያግራልን፡፡

---

1) እሳቸው ዓብዱራህማን ኢብኑ ሙሐመድ ኢብኒል ሐሰን ኢብኒ ሂበቲሏህ ኢብኒ ዓብዲሏህ ኢቢኒል ሑሰይን አድዲመሽቂይ፤ ፈኽሪዲን ኢብን ዓሳኪር በመባል የሚታወቁ ታዋቂው የሻፊዒይ ፈቂህ ናቸው፡፡ በ500 ሒ ተወለዱ፡፡ በመካ፣ በደማስቆ፣ በቁድስና በሌሎች አገሮች ስተምረዋል ሐዲስም አስተላልፈዋል፡፡ አያሌ ታዋቂ ዓሊሞች አሞግሷቸዋል፡፡ ታጁዲን አስሱብኪይ ጠበቃቱ አሸሻፊዒያ በተሰኘ መፅሐፋቸው እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹የዘመናቸው ሰዎች በአእምሮአቸውና በዲናቸው ታላቅ እንደሆኑ ተስማምተዋል፡፡›› አሏህ ይዘንላቸውና ያረፉትም በረጀብ ወር በ620 ሒ ነው፡፡ የተቀበሩትም ደማስቆ በሚገኘው በሱፊዮች መካነ መቃብር ነው፡፡ ጠበቃቱ አሸሻፊዒያን (177/8) ተመልከት፡፡

ትንታኔ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

አንተ የእውቀት ፈላጊ ሆይ! (**አሏህ እኛንም ሆነ አንተን**) ሐቅን ለማወቅና ትክክለኛን ነገር እንድንገጥም (**ወደ ቀና መንገድ ይምራን። ሀያሉና ታላቁ ፈጣሪያችን አሏህ በንግስናው**) ማለትም በስልጣኑ አጋር የሌለው[2] (**ብቸኛ መሆኑን በተጠያቂዎች ሁሉ ማወቁ**) እና ማመኑ (**ግዴታ መሆኑን እወቅ።**) ለዚህ ዓለም ከአሏህ በስተቀር ሌላ ጌታና ፈጣሪ የለውም። ካለ እርሱ በስተቀር ሊገዙት የሚገባው ሌላ የለም። ተጠያቂ ሲባል ለአካለ-መጠን የደረሰ፤ እብድ ያልሆነና፤ የእስልምና መሠረታዊ ጥሪ የደረሰው ማለትም ካለ አሏህ በስተቀር ሌላ ፈጣሪ እንደሌለና ሙሐመድ ﷺ የአሏህ መልእክተኛ መሆናቸው የደረሰው ሰው ነው።

(**ዓለምን በጠቅላላ**) ማለትም ካለመኖር ወደ መኖር የገባ ማንኛውም ነገርን የፈጠረው አሏህ ነው ። ይህ ሲባል የዓለም (**ላይኛውን**) ክፍል እሱም ሰማያትና ከነሱ በላይ ያሉትን እንደ ጀነት ያሉ (**እና፤ ታችኛውን ክፍል**) እሱም ምድሮችና ከነሱ በታች ያሉትን አንደ ጀሃነም ያሉ ዓለማትን (**ማለትም ዓርሽና ኩርስይን፣**) ሰባቱ (**ሰማያትንና መሬትን፣ ውስጣቸውና መካከላቸው ያለውን ሁሉ ፈጠረ።**) ዓርሽ የጀነት ጣሪያ ነው። ከፍጥረታቶች ሁሉ በግዝፈት ትልቁ ሲሆን፤ አራት እግር ያለው ትልቅ ዙፋን ነው። ኩርሲይ ደግሞ ከዓርሽ በታች የሆነ ትልቅ አካል ሲሆን፤ ከሰማያትና ከመሬት የተለቀ ከዓርሽ ያነሰ ነው። ሰማያትና መሬት ውስጥ ሲባል እንደ መላኢካዎች፣ ሰዎችና፣ አጋንንቶችና ሌሎችን ሲያካትት፤ በመካከላቸው ያለ ሲባል ደግሞ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብቶችንና ሌሎችንም ያካትታል። ይህ ደግሞ የባሮችን አካልና ስራዎቻቸውን እንዲሁም

---

2) ሼኽ ጀማሉዲን አልአኒይ አሏህ ይዘንላቸውና እንዲህ አሉ፦ «አሏህ በእውኑ፣ በባህሪውና፣ በድርጊቱ አምሳያ የለውም፤ ለእርሱ አጋር የለውም።» ኪፋየቱጣሊቢን በተሰኘ መፅሐፋቸው (ገፅ-3) ጠቅሰውታል።

ንግግራቸውን፣ ልቦናዊ ሽውታቸውን[3]፣ ማረፊያ ቀናቸውን፣ ሲሳያቸውና ማንኛውም የሚከሰትላቸው ወይም የሚከሰትባቸው ነገሮችን ሁሉ ያካትታል። ምክንያቱም ይህ ሁሉ የዓለም ከፊሉ ስለሆነ ነው። አሏህ በቁርኣን እንዲህ ብሏል፡- ﴿وَخَلَقَ كُلَّ شَيۡءٖ﴾ ማለትም ካለመኖር ወደ መኖር አስገኝቶታል።

እንዲሁም እንዲህ ብሏል፡- ﴿هَلۡ مِنۡ خَٰلِقٍ غَيۡرُ ٱللَّهِ﴾ ማለትም በዚህ ዓለም ለማንኛውም ነገር ካለ አሏህ በስተቀር ሌላ ፈጣሪ የለም። የዚህች ዓለም መኖር ለአሏህ መኖር ማስረጃ ነች። ምክንቱም በጭንቅላታችን ስናስበው አንድ ድርጊት ያለ አድራጊ ሊኖር አይችልምና ነው።

(**ሁሉም ፍጥረታቶች**) አካላቶችም ሆኑ ባህሪያት (**በችሎታው ቁጥጥር ሥር ናቸው።**) ማለትም የተገኙት በችሎታው ነው። እነሱም በቁጥጥሩ ሥር ናቸው፡ ፡ እንደፈለገው ማድረግ ይችላል። ከዓለም ውስጥ (ብናኝም ብትሆን ካለ እርሱ ትእዛዝ) እና መሻት (**አትንቀሳቀስም።**) ብናኝ ስንል የፀሐይ ብርሃን በመስኮት ሲገባ የሚታይ ነገር ነው። (**ከእርሱ ጋር**) የ(**ፍጡርን**) ጉዳዮች በማስተዳደር አጋር ሆኖ (**የሚያስተዳድር የለም።**) የሁሉም ፍጡር አስተዳዳሪ እርሱ ነው። ማለትም በዚህ ዓለም የሚከናወነውን ሁሉ የወሰነ ነው። (**በንግስናውም**) ከእርሱ ጋር (**አጋር የለውም።**) ምክንያቱም በዚህ ዓለም ላለው ሁሉ እውነተና ባለቤት እርሱ ብቻ ነው።

አሏህ (**ሕያው**) ነው አይሞትም። ሕይወቱ የኛን ሕይወት አይመስልም። በመንፈስ በስጋና በደም አይደለም። (**እንዲሁም በእራሱ የተብቃቃ፤**) ማለትም ከእርሱ ሌላ የሆኑ ሁሉ ከእርሱ ሲከጅሉ፤ እርሱ ግን ከሌላ ፈላጊ አይደለም። (**ማንቀላፋትም**) ማለትም እንቅልቻም (**ሆነ እንቅልፍም አይወስደውም።**) ምክንያቱም በፈጣሪ የማያመች ሊኖር የማይችል ጎዶሎነትን ስላዘሉ ነው።

አሏህ (**የተደበቀውንም**) ማለትም ከፍጥረታቶች የተደበቀና የተሰወረውን የሚያውቅ ነው። ፍጥረታቶች ግን ከአሏህ እውቀት የሻላቸውን ያህል እንጂ ሁሉንም አያካልሉም። አሏህ የተሰወረውንም (**ሆነ የሚታየውንም**) ማለትም ፍጥረታቶች የሚያዩትንም (**የሚያውቅ ነው። በምድርም**) እንዲሁ ከስሯ

---

3) ሼኽ ጀማሉዲን አልአኒይ ለዚህ ማስረጃ ﴿وَٱللَّهُ خَلَقَكُمۡ وَمَا تَعۡمَلُونَ﴾ የሚለውን አያ አስፍረው እንዲህ አሉ፡- «ይህች አያ ባሮችና ድርጊቶቻቸው በጎም ሆነ መጥፎ ለሀያሉ ጌታችን ፍጥረታት እንደሆኑ አስፍራለች። ለቀደሪዮችም ምላሽ ሰጠች።» ኪፋየቱጣሊቢን መፅሐፍን (ገፅ-4) ተመልከት።

የሉትንም (**ሆነ በሰማይ**) እንዲሁ ከሱ በላይ ያሉት (**ምንም አይሰወርበትም።**) የተጥራራው ጌታችን ሁሉንም ነገር ባጠቃላይም ሆነ በዝርዝር ያውቃል። አሏህ አካሎችንና ባህሪያቶችን፤ ባሪያዎችንና ስራዎቻቸውን፤ ውጫዊ ገጽታቸውንና ውስጣቸውንም ያውቃል። እንዲሁም እንደ እፅዋትና እንስሶች ያሉትን (**በየብስና በባህር ውስጥ**) ደግሞ እንደ ልዑል (**ያለውን ያውቃል። አንዲትም ቅጠል ብትሆን አትወድቅም እርሱ ሳያውቃት። አንዲትም ፍሬ ብትሆን ጨለማ መሬት ላይ፣**) ማለትም በምድር ውስጣዊ ክፍል አይኖርም አሏህ ቢያውቀው እንጂ። (**እርጥብም ሆነ ደረቅ አይኖርም**) እርሱ ሳያውቀው። አንድም ሰው አይወለድም፤ አንድም ጠብታ ከሰማይ አይወርድም አሏህ ሳያውቀው። ይህ ሁሉ ደግሞ አይኖርም (**ለውሐል ማህፉዝ ውስጥ**) ተጽፎ (**ቢኖር እንጂ።**) ለውሐል ማህፉዝ ከሰባተኛው ሰማይ በላይ የሚገኝ ግኡዝ አካል ሲሆን ከዚህ በፊት የነበረውንና ወደ ፊት እስከ የውመል ቂያማ የሚሆነውን የተጻፈበት ነው።

አሏህ (**ሁሉንም ነገር በእውቀቱ አካቷል።**) የተቀደሰው ጌታችን ከዚህ በፊት የተከሰተውን፤ አሁን የሚሆነውንና፤ ወደፊት የሚከሰተውንም መጀመሪያ በሌለው፣ ፍጡር ባልሆነው፣ አምሳያ በሌለው፣ በማይቀያየረው፣ በማይጨምረውና፣ በማይቀንሰው እውቀቱ ያውቃል። ለአሏህ አንድን ነገር ሳያውቀው ቀርቶ እለሱ አዲስ እውቀት አይከሰትበትም። መርሳትም ቢሆን አይከሰትበትም።

(**የሁሉንም ነገር ብዛት ያውቃል።**) የተቀደሰው ፈጣሪ መጀመሪያ በሌለው እውቀቱ የሁሉንም ነገር ብዛት ያውቃል። እርሱ የፍጥረታትን ትንፋሽ ብዛት ያውቃል። እንዲሁም የዝናብ ጠብታዎች፣ የአሸዋ ጠጠሮችንና የሌሎችንም ብዛት ያውቃል።

አሏህ (**ያሻውን የሚያደርግ፤**) ነው። ማለትም እንዲገን የፈለገውን መገኘቱን በፈለገው ወቅትና መገኘቱን በፈለገው ባህሪ የማስገኘት ችሎታ አለው። (**በሚፈልገው ነገር ላይ ችሎታ አለው።**) እንዲገኝ የፈለገውን ነገር መፍጠር አይሳነውም። ማንም የሚከለክለውም የለም። የአሏህ መልእክተኛው ﷺ እንዲህ አሉ፦- "مَا شَاءَ اللهُ كَانَ وَمَا لَمْ يَشَأْ لَمْ يَكُنْ" ማለትም፦ «አሏህ ያሻው ይሆናል።

ያላሻው ደግሞ አይሆንም።››[4] ማንኛውም ነገር ኸይርም ሆነ ሸር አሏህ መኖሩን የሻው ከሆነ ካለመኖር ወደ መኖር ይሻገራል። ነገር ግን ኸይሩ በአሏህ ውዴታና ትእዛዝ ሲሆን፤ ሸሩ ግን በአሏህ ውዴታና ትእዛዝ አይደለም። ማንኛውም ነገር አሏህ መኖሩን ያልፈለገው ከሆነ በማንም ዱዓእ ይሁን ሰደቃ ካለመኖር ወደ መኖር አይሻገርም። ከኃጢያት አንርቅም በእርሱ ጥበቃ ቢሆን እንጂ፤ በጎን ነገር መስራት አንችልም በእርሱ እገዛ ካልሆነ በስተቀር።

የተጥራራው ጌታችን የማይጠፋና ማንም የማይቀናቀነው (**ንግስናም አለው እንዲሁም በራስ መብቃቃት።።**) ከፍጥረቱ ምንም አይፈልግም። እነሱ ግን ከእርሱ ይከጅላሉ። ከነሱ ለራሱ ምንም ጥቅም አያስገኝም። ከራሱም አደጋን በነሱ አይከለክልም። (**የማይበገር ሀይልም አለው።።**) እርሱ የማይሸነፍ ሃያል ነው። (**እንዲሁም ዘላለማዊነት**) አለው አይጠፋም፣ አይሞትም፣ አይባክንም። (**ፍርድም አለው**) ማለትም ገደብ የሌለው ማዘዝና መከልከል፤ (**አንዲሁም ውሳኔ**) አለው። ማለትም መፍጠር የእርሱ ነው። ይኸውም አንድን ነገር ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት ነው። እንደ አርራህማንና አርረሂም ያሉ ምሉእነትን የሚያመላክቱና ለእርሱ ተገቢ የሆኑ (**መልካም ስሞችም አሉት።።**) ከጎዶሉ ባህሪያት ሁሉ የጠራ ነው። ለዚህም ነው እርሱን ኣህ ወይም ሩህ ወይም ዓቅል ብሎ መጥራት የማይፈቀደው።

(**የወሰነውን የሚመልስ የለም።።**) ማንም ቢሆን እርሱ የወሰነውን የሚመልስ የለም። (**የሰጠውንም የሚከለክል የለም።።**) ማንም ቢሆን እርሱ የለገሰውን ሲሳይ የሚከለክል የለም።

አሏህ (**በፍጥረቱ የፈለገውን ያደርጋል።።**) የሚያደርገውም በምርጫው እንጂ ሳይወድ በግድ አይደለም። አሏህ (**ፍጥረቱ ላይ በሚፈልገው ይፈርዳል።።**) የፈለገውን መልካም ሲያደርግ፤ የፈለገውን አስቀያሚ ያደርጋል። የፈለገውን ግዴታ ሲያደርግ፤ የፈለገውን ሐራም ያደርጋል።

ከፍጥረቱ (**ምንዳም**) ሆነ ጥቅም (**አይጠብቅም።።**) ከነሱ (**ቅጣትም**) ሆነ ጉዳት (**አይፈራም።።**) የተቀደሰው ጌታችን (**በእርሱ ላይ ግዴታም ሆነ**) ሐቅ የለበትም። ። ምክንያቱም ምንም ግዴታ የለበትም[5]። እንዲሁም በእርሱ (**ፍርድ የለበትም።**

---

4) አቡዳውድ ሱነናቸው ውስጥ የአደብ ክፍል ላይ ሲነጋ ስለሚባለው በተጠቀሰበት ምእራፍ ላይ ዘግበውታል።

5) የሼኽ አኒይን መፅሐፍ ኪፋየቱጣሊቢን (ገፅ-3) ተመልከት።

፡) ምክንያቱም በእርሱ የሚፈርድ የለም፡፡ እርሱን የሚያዝም ሆነ የሚከለክል ስለሌለ ነው፡፡

አሏህ አንድን ሰው የሚቸረው (**ፀጋዎች ሁሉ ከእርሱ ችሮታ ነው**) እንጂ ግዴታ አይደለም፡፡ በአንድ ሰው የሚያወርደው (**ቅጣቶቹ ሁሉ ከእርሱ ፍትህ ነው**) እንጂ በደል አይደለም፡፡ አሏህ ምንዳ የሰጠው ችሮት ሲሆን፤ የቀጣው ደግሞ ከፍትሃዊነቱ ነው፡፡ ﴿وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّٰمٍ لِّلۡعَبِيدِ﴾ ማለትም ‹‹ፈጣሪህ ባሮቹን በዳይ አይደለም፡፡››

የተቀደሰው ፈጣሪ በባሪያዎቹ ላይ (**በሚሰራው አይጠየቅም፡፡**) ምክንያቱም እነሱም ሆኑ ንብረቶቻቸው የአሏህ ስለሆኑ እንደፈለገ ማድረግ ይችላል፡፡ (**እነሱ ግን ይጠየቃሉ፡፡**) ባለቤት ለሆኑለት ድርጊትም ሒሳብ ይደረጋሉ፡፡

አሏህ (**ከፍጥረታት በፊት የነበረ ነው፡፡**) የአሏህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡- "كَانَ اللهُ وَلَمْ يَكُنْ شَيءٌ غَيْرُهُ" ‹‹አሏህ ከእርሱ ሌላ ምንም ነገር ሳይኖር ነበር[6]፡፡›› ማለትም ከአለማት ምንም ነገር ሳይኖር አሏህ ጥንት ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር ውሃም ሆነ አየር፣ ጊዜም ሆነ ቦታ፣ መሬትም ሆነ ሰማይ፣ ዓርሽም ሆነ ኩርሲይ፣ ብርሃንም ሆነ ጨለማ፣ ሰውም ሆነ ኢጋንንት፣ መላኢካዎችም ቢሆን አልነበሩም፡፡ እንዲሁም ለእርሱ ጅማሬ ስለሌለው ለባህሪያቶቹም ጅማሬ የላቸውም፡፡ ለዚህም ነው ጥንት ያልነበረ ባህሪ አይከሰትበትም፡፡ ምክንያቱም በአንድ ነገር ላይ የሁኔታዎች መቀያየር የግኝትነቱ ትልቅ ምልክት ነው፡፡ እንዲሁም (**ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ የሚባል የለውም፡፡**) ማለትም የእርሱን መኖር አለመኖር አልቀደመውም፡፡ ስለዚህ በመኖር እንዲወሰን ያደረገው የለም፡፡ ከእርሱ በስተቀር ያሉ ዓለማቶች ግን ግኝቶች ናቸው፡፡ መኖራቸውን አለመኖር ቀድሞታል፡፡ ለዚህም ነው ካለመኖር ይልቅ በመኖር እንዲወሰኑ የሚያደርጋቸው ያስፈለጋቸው፡፡ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ የሚባል የለውም፡፡ ስለዚህ መጥፋት አይከተለውም በእርሱም አያመችም፡፡ የተቀደሰው አሏህ በስድስቱ አቅጣጫዎች አይወሰንም፡፡ ስለዚህ (**ላይም ሆነ ታች፣ ቀኝም**

---

6) ቡኻሪይ በሰሂሃቸው የፍጥረታት ጅምር ክፍል፤ ﴿وَهُوَ ٱلَّذِى يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ﴾ ስለሚለው አንቀፅ የወረደውን በሚመለከት ምእራፍ ዘግበውታል፡፡ በይሃቅይ ደግሞ ሱነኑል ኩብራ (3/9) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሆነ ግራ፣ ፊትም ሆነ ጀርባ የለውም።) ምክንያቱም አቅጣጫዎች የዚህ ዓለም ክፍል ናቸው። አሏህ ደግሞ ከዓለማቶች ምንም አይከጅልም[7]።

የተጥራራው ጌታችን (**የዓለም አጠቃላይም ሆነ ከፊሉም አይደለም።**) ማለተም ዓለም በጠቅላላ አሏህ አይደለም። እንዲሁም የዓለም ከፊል አካልም አይደለም። በእርሱ ውስጥ የሚሆን ነገር የሚባል የለም። እርሱ ደግሞ በሌላ ነገር ውስጥ በፍፁም አይሆንም። ምክንያቱም መባዛትን፣ መበራከትን፣ መከፋፈልንና፣ መገማመስን ስለሚያስከትል ነው። ይህ ደግሞ በአካላቶች የተወሰኑ ባህሪያት ናቸው። አሏህ ደግሞ አካል አይደለም[8]። እርሱ እንደ ቅንጣት ከጥቂት ክፍልፋዮች የተገነባ ትንሽ አካልም ሆነ፤ እንደ ዓርሽ[9] ከብዙ ክፍልፋዮች የተገነባ ግዙፍ አካልም አይደለም። እንዲሁም እንደ ዛፍ፣ ድንጋና ሰው ያለ የሚዳሰስ ግዑዝ አካልም ሆነ፤ እንደ ብርሃን፣ ነፍስ፣ አየር፣ አጋንንትና መላኢካዎች የማይዳሰስ ረቂቅ አካልም አይደለም። ምክንያቱም ፍጥረታቶቹን በፍፁም ስለማይመስል ነው።

አሏህ (**መቼ ነበር አይባልም።**) ምክንያቱም ለመኖሩ ጅማሬ የለውምና። እንዲሁም አሏህ (**የት ነበርም ሆነ እንዴት ነበር አይባልም።**) የት ነበር የማይባለው ቦታ ስለሌለው ነው። መሬትም ሆነ ሰማይ ላይ፤ ዓርሽም[10] ላይ ሆነ በታች፤ የትም ቦታ ሆነ ሁሉም ቦታ አልሰፈረም። ይልቁንስ የተጥራራው አሏህ ያለ ቦታ ያለ ነው። የአሏህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

"وَأَنْتَ الظَّاهِرُ فَلَيْسَ فَوْقَكَ شَيءٌ وَأَنْتَ البَاطِنُ فَلَيْسَ دُونَكَ شَيءٌ"

---

7) ኢማም አቡ ጃዕፈር አጥጠሃዊይ በ227 ሒ የተወለዱት የአህሉሱና ወልጀማዓ እምነት ማብራሪያ ነው በማለት ባዘጋጁት የዓቂዳ መፅሀፋቸው ላይ እንዲህ አሉ፡- «እንደተቀሩት ግኝቶች ስድስቱ አቅጣጫዎች አያካልሉትም።»

8) ሼኽ አኒይ አሏህ ከአካልነት፣ የሌለ ነገር ከመሆንና፣ አንድ ነገር ውስጥ ከመሆን የተጥራራና የተቀደሰ መሆኑን ጠቅሰዋል። ኪፋየቱጣሊቢንን (ገፅ-2) ተመልከት።

9) ኢማም ዓሊይ አሏህ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ አሉ፡- «ጌታችን ውስን የመሰለው የሚመለከውን ፈጣሪ የማያውቅ ነው።» አቡ ኑዓይም ሂልየቱል አውሊያእ በተሰኘው መፅሐፋቸው (1/73) ዘግበውታል። ኢማም አቡ ጀዕፈር አጥጠሃዊይ ደግሞ እንዲህ በለዋል፡- «አሏህ ከወሰኖች፣ ከጫፎች፣ ከጎኖች፣ ከትላልቅ የሰውነት ክፍሎችና፣ ከትናንሽ የሰውነት ክፍሎች የተጥራራ ነው።»

10) ኢማም ዓሊይ አሏህ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ አሉ፡- «የተጥራራው አሏህ ዓርሽን የፈጠረው ችሎታውን ሊያሳይ እንጂ ቦታ አድርጎ ሊይዘው አይደለም።» ኢማም አቡመንሱር አልበግዳዲይ አልፈርቅ በይነል ፊረቅ በተሰኘው መፅሐፋቸው (ገፅ-333) ዘግበውታል። ሼኽ አብዱልገኒይ አናብሉሲይ ደግሞ እንዲህ አሉ፡- «አሏህ ሰማያትንና መሬትን የሞላ ነው ብሎ የሚያምን ወይም ዓርሽ ላይ የተቀመጠ አካል ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ ሙስሊም ነኝ ብሎ ቢያስብም ካፊር ነው።» ፈትሁርረባኒ በተሰኘ መፅሐፍ (ገፅ-124) ጠቅሰውታል።

«አንተ ነህ አዝዛሂር ከአንተ በላይ ምንም ነገር የለም። አንተው ነህ አልባጢን ከአንተ በታች ምንም ነገር የለም[11]።» እንዲሁም አሏህን እንዴት ነው አይባልም። ምክንያቱም እንዴት የሚባለው እንደ ግኝትነት፣ መቀየር፣ መለወጥ፣ ምስል፣ መልክ፣ ርዝመት፣ እጥረት፣ ቀለም፣ እንቅስቃሴ፣ እርጋታና፣ መቀመጥን[12] ለመሳሰሉ ለፍጥረታት ባህሪያቶች ነው። የተጥራራውና የተቀደሰው ፈጣሪያችን ካፊሮች ከሚሉት የላቀና የጠራ ነው።

የዚህ መትን ባለቤት እነዚህን የመሰሉ ቃላቶችን ለአሏህ እንዳንጠቀም ከከለከሉ በኋላ የእውነት ባለቤቶች እምነትን በማስጨበጥ እንዲህ አሉ፦ አሏህ ጥንት (**ቦታ ሳይኖር ነበር።**) ማለትም ቦታ የሚባል አልነበረም። ከዛ በኋላ (**ፍጥረታቶችንም ከወነ።**) ማለትም ዓለማትን ከፈጠረም በኋላ ያለ ቦታ ነው ያለው። ምክንያቱም አሏህ ከአንድ ሁኔታ ወደ ሌላ ሁኔታ መቀያየር አያመችበትምና[13]። የተቀደሰው አሏህ (**ዘመንንም አበጀ። በዘመን አይታጠርም።**) ስለዚህ ዘመን አያልፍበትም። ከጉድለት የተጥራራው አሏህ (**በቦታም አይወሰንም።**) ምክንያቱም ባዶ ቦታ የሚይዝ አካል ስላልሆነ ነው። አሏህ እንደ ብርሃንና አየር አንድን ክፍል ወይም መስጂድን ወይም ካዕባን ወይም ህዋን የመሰለ ቦታን የሚሞላ አይደለም።

ከዚህ በመነሳት ማንኛውም በቁርአን ወይም በሐዲስ የሰፈረ ላይ ላዩ ሲታይ ለአሏህ ቦታ እንዳለው አድርጎ የሚያስመስል ከሆነ ታእዊል ማድረጉ ግዴታ ይሆናል። ማለትም በውጫዊ ትርጉሙ ሳይሆን አሏህ ከቦታ የተጥራራ መሆኑን

---

11) ሙስሊም በሰሒሓቸው የዚክርና የዱዓእ ክፍል ውስጥ እንቅልፍ ጊዜ መተኛ ላይ ሲያርፉ ስለሚባለው በተመለከተ ምእራፍ ዘግበውታል። በይሃቂይ ይህን ሐዲስ ከጠቀሱ በኋላ እንዲህ አሉ፦ «ከእርሱ በላይ ምንም ነገር ከሌለ፤ ከእርሱም በታች ምንም ነገር ከሌለ ቦታ ላይ አይደለም ማለት ነው፡፡» አልአስማእ ወስሲፋት በተሰኘው መፅሐፍ (ገፅ-400) ጠቅሰውታል።

12) ኢማም አቡ ጀዕፈር አጥጠሓዊይ በዓቂዳ መፅሐፋቸው እንዲህ አሉ፦ «አሏህን ከሰው ባህሪ በሆነ አንድ ባህሪ የገለፀ ከእስልምና ይወጣል።» አቡ ሱለይማን አልኸጣቢ ደግሞ እንዲህ አሉ፦ በእኛም ሆነ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ የሚሆንብን ፈጣሪያችን የምስልም ሆነ የቅርፅ ባለቤት እንዳልሆነ ማወቅ ነው። ምክንያቱም ምስል እንዴታን ያስከትላል። እንዴታ ደግሞ ለአሏህም ሆነ ለባህሪያቱም ተገቢ አይደለም።» ይህንንም በይሃቂይ በአስማእ ወስሲፋት (ገፅ-296) ዘግበውታል።

13) ኢማም ዓሊይ አሏህ ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ አሉ፦ «አሏህ ቦታ ሳይኖር ነበር። አሁን ደግሞ እርሱ እንደነበረው ያለ ነው።» አቡ መንሱር አልበግዳዲይ አልፈርቅ በይነል ፊረቅ በተሰኘው መጽሐፋቸው (ገፅ-333) ዘግበውታል።

ከሚያመላክቱ ሙሕከማት የቁርኣን አያዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ይፈሰራል[14]::

የተቀደሰው ፈጣሪያችን ጉዳዮችን ሲፈፅም (**አንድ ጉዳይ ከሌላ ጉዳይ አይጠምደውም::**) ምክንያቱም አንድን ነገር የሚያደርገው ማለተም ካለመኖር ወደ መኖር የሚያመጣው ጅማሬ በሌለው ችሎታውና ፍላጎቱ፤ መሳሪያ መጠቀም ሳያስፈልገው እንዲሁም በሰውነት ክፍል አካሎች ሳይታገዝ ወይም ከምንም ነገር ጋር ንክኪ ሳይኖረው፤ ምንም ችግር ሳይደርስበት ነው::

የተጥራራው ጌታችን (**ሐሳብ አይደርስበትም::**) ምክንያቱም ሐሳብ የሚያጠነጥነው አንድ ሰው በለመደው በስሜት ህዋሱ በሚያውቀው እንደ መጠን፣ ቅርፅ፣ ቀለምና፣ ቦታ ያለውን ነገር ስለሆነ ነው:: አሏህ ደግሞ በዚህ አይገለፅም:: (**ልቦናም አያካልለውም::**) ማለትም በልቦናዎች አይታጠርም:: (**በጭንቅላት ውስጥም አይወሰንም::**) ስለዚህ ጭንቅላቶች ሊመስሉት አይችሉም:: (**በነፍስም ውስጥ አይመሰለም::**) ምክንያቱም የተጥራራው ፈጣሪያችን አምሳያ የለውምና:: (**በሐሳብም አይሳልም::**) ምክንያቱም ምስል የለውምና:: (**በልቦናም እንዴት ተብሎ አይታሰብም::**[15]) ምክንያቱም እንዴት የሚያስብል የለውምና:: (**ሐሳብም ሆነ ቅዠት አይደርስበትም::**) ማለትም የአሏህን እውነታ አይደርሱበትም:: ምክንያቱም የአሏህን እውነታ ካለ እርሱ በስተቀር ሌላ የሚያውቅ ማንም የለምና[16]:: ለዚህም ነው ሰለፎች ስለ አሏህ እውን ማሰላሰል የከለከሉት:: ኢማም የሆኑት ዙኑን አልሚስሪይ እንዲህ አሉ:- "مَهْمَا تَصَوَّرْتَ بِبَالِكَ فَاللهُ بِخِلافِ ذَلِكَ" ‹‹የፈለከውን ያህል በሐሳብህ ብትስልም፤ አሏህ እሱን አይመስልም[17]::›› ምክንያቱም ማንኛውም በሐሳብህ የምትስለው

---

14) ሱፍይ የሆኑት አልኢማም አህመድ አርሪፋዒይ እንዲህ አሉ:- « ሙተሻቢህ በሆኑ የቁርኣን አያዎችንና ሐዲሶችን ውጫዊ ትርጉማቸውን የሙጥኝ ባለመያዝ እምነታችሁን (ዓቂዳችሁን) ጠብቁ:: ምክንያቱም ይህን ማድረግ እርግጥ የከህደት መሠረት ነውና::» ቡርሃኑል ሙአየድ መጽሐፋቸው ውስጥ (ገፅ-22) ጠቅሰውታል::

15) አሸይኽ አልአኒይ እንዲህ አሉ:- «ልቦናዎችም እንዴት ብለው አያስቡትም::» ኪፋየቱጣሊቢንን (ገፅ- 2) ተመልከት::

16) ሱፍይ የሆኑት አህመድ አርሪፋዒይ እንዲህ አሉ:- «የአሏህን ማወቅ መጨረሻ ሲባል የተጥራራው አሏህ ያለ ቦታና ያለ እንዴታ መሆኑን ማረጋገጥ ነው::» በሒከም መጽሐፋቸው (ገፅ-36) ጠቅሰውታል::

17) አልሓፊዝ ኢብን ዐሳኪር ታሪኽ ዲመሽቅ በተሰኘው መጽሐፍ (ቅፅ-17/ገፅ-404) ዘግበውታል:: አሸይኹል አኒይ ደግሞ ከኢማም አቢ ኢስሓቅ አልአስፈራዩኒ የሚከተለውን አስተላልፈዋል:- «የሐቅ ባለቤቶች ስለ ተውሂድ የተባለውን በጠቅላላ በሁለት ንግግር ሰበሰቡት:: አንደኛው:- በሐሳብ የሚሳል የተጥራራው አሏህ እሱን እንደማይመስል ማመን:: ሁለተኛው:- የአሏህ እውኑ (ዛቱ) ከማንኛውም

ፍጡር ነው፡፡ ፈጣሪ ደግሞ ፍጡሩን በምንም አይነት አይመስልም፡፡ እውኑ የፍጥረታቱን እውን አይመስልም፡፡ ባህሪየቶቹ የፍጥረታቱን ባህሪየቶች አይመስልም፡፡ ድርጊቱም የፍጥረታቱን ድርጊት አይመስልም[18]፡፡ ይኸውም የተቀደሰው የቁርኣን አያ ﴿لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞ﴾ እንዳመላከተን ነው፡፡ ማለትም **(እርሱን የሚመስል በጭራሽ የለም፡፡)**

አሏህ በዚህ አያ ﴿وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ﴾ ማለትም **(እርሱ ሰሚም ተመልካችም ነው)** ከማለቱ በፊት ከፍጥረታት የተጥራራ መሆኑን አስቀደመ፡፡ ምክንያቱም የእርሱ መስማቱና ማየቱ የፍጥረቱን መስማትና ማየት እንዳይመስለን ነው[19]፡፡ የተጥራራው ጌታችን ድምፆችን ሁሉ መጀመሪያ በሌለው መስማቱ ያለ ጆሮ እገዛና ያለ ምንም መሳሪ ይሰማል፡፡ እንዲሁም የሚታዩትን ሁሉ መጀመሪያ በሌለው ማየቱ ያለ ዓይን ብሌን እገዛና ያለ ብርሃን ጨረር ያያል፡፡

የተቀደሰው አሏህ አምሳያ፣ መጀመሪያና፣ መጨረሻ በሌለው ንግግሩ ይናገራል፡፡ ንግግሩም የሚጀመርና የሚጨረስ ያልሆነ፤ ፊደል፣ ድምፅና፣ ቋንቋም አይደለም[20]፡፡ ነገር ግን በሰይዳችን ሙሐመድ ﷺ የወረደው ቁርኣን የአሏህን መጀመሪያ የሌለው ንግግሩን የሚያመላክት ነው፡፡ ለዚህም ነው የአሏህ ንግግር በማለት የሚጠራው፡፡ ማንም ሰው ሆነ መላክ የፃፈው ድርሰት አይደለም፡፡

የዓቂደቱል ሙርሺዳህ የቃላት ፍቺ አሏህ አግርቶልን፤ እርሱን በማመስገን

እለተ ሐሙስ በዘጠነኛው (9) የጁማደል አወል ወር

በሺ አራት መቶ ሰላሳ አራት (1434)

አመተ ሂጅራ ተጠናቀቀ፡፡

አውን (ዛት) ጋር እንደማይመሰልና ከባህሪያቶቹም የማነፈግ አይደለም፡፡ (ባህሪያት አልባም አይደረግም፡፡)» ኪፋየቱጣሊቢንን (ገፅ-4) ተመልከት፡፡

18) አሸይኽ አልአኒይ እንዲህ አሉ፡- «አሏህ በምንም ረገድ በእውኑም ሆነ በባህሪያቱም እንዲሁም በድርጊቶቹም ፍጥረታትን አለመምሰሉ ለእርሱ ተገቢ ነው፡፡» ኪፋየቱጣሊቢንን (ገፅ-3) ተመልከት፡፡

19) የዚህ አንቀፅ መጀመሪያ ለሙሽቢሆች (አሏህን ከፍጥረታት ጋር ለሚያመሳስሉትን) ምላሽ ነው ሲሆን፤ መጨረሻው ለሙዓጢሎች (የአሏህን ባህሪ ለሚክዱት) ምላሽ ነው፡፡ አንቀፁ በጠቅላላ ደግሞ የተውሂድን ጭማቂ ብያኔ ይሰጣል፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን አናሳ ቃለቶቹ ቢሆኑም ነገር ግን የተውሂድ ጉዳዮችን ስብስብ ያጠቃለለ ነው፡፡»

20) አሸይኽ አልአኒይ እንዲህ አሉ፡- «እንደ ድምፅና ፊደል እንዲሁም መቅደምና መዘግየትን ከመሰሉ ከፍጡር ባህሪያት የተጥራራ ንግግር ለአሏህ ተገቢ ነው፡፡» ኪፋየቱጣሊቢንን (ገፅ-3) ተመልከት፡፡